የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ

ETHIOPIAN PEOPLE'S PATRIOTIC FRONT

GUARD

# ብልሹ አገዛዝ ያመጣው ትልቅ የታሪክ ዝቅጠት

ሃገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰአት ታይቶ በማይታወቅ የባሰ ሁኔታ ላይ መሆንዋን የተገነዘብነው ጉዳይ ሆንዋል። ህዝባችንን ለከፍተኛ ሃዘንና ሰቆቃ የዳረገው ይህ በተለያዩ የአረብ ሃገራት በሳውድአረብያ እንዲሁም እንደ ግብጽ ሊብያ እና ሱዳን ባሉ የአፍሪካ ሃገራት ላይ በወገናችን ላይ እየደረሰ ያለው ኢሰብአዊ ድርጊት በመባባሱ የሃገራችን ህዝቦች ህልውና ምን ያህል ያከተመለት ደረጃ ላይ መድረሱን እያሳየን ነው።

በኛ ሃሳብ ሃገራችን ኢትዮጵያ በታሪክ ለመጀመርያ ጊዜ መሪና ጠባቂ እንደሌላት ያሳየችበት ወቅት መሆኑን በግልጽ አመላክቷል። የወያኔ መንግስት ጸረ ዴሞክራሲያዊ ሆኖ የስልጣን ክፍፍል እንዳይኖር ህግ አውጭው፣ ህግ አስፈጻሚው፣ህግ ተርጓሚው በአንድ ማእከል ተተብትቦ ሰው ሃሳቡን እንዳይናገር እንዳይሰራ ዘርቶ እንዳያጭድ ነግዶ እንዳያተርፍ በሃገሩ ላይ እንደ ሳውድ አረብያ ህንድ እና ቻይና ነግሶ መሬቱ ተነጥቆ በቅየው፣ በመንደሩ እንዲሁም በሃገሩ እንዳይኖር በማድረግ ስርአቱን በማቆሸሽ ሃገሪትዋን ወደ አዘቅት በመጣል አምባ ገነን ስርአት በኢትዮጵያ ላይ አስፍኖ ህገ መንግስቱን ከወረቀት ያላለፍ መቀለጃ አርጎት ይገኛል።

የሃገራችን ወጣት ወንዶች እና ሴት ልጆች ሃገር መለወጥ የሚችለውን አፍላ ጉልበት ይዘው ሃገራቸው እንጥፍጣፊ ተስፋ ቢያጡ ለበርሃና ለስደት ተዳርገው ግማሹ ለባህር ግማሹም ለበርሃ ሲሳይ ሆነው የተቀሩት ደግሞ በሰው በላ ሽፍቶች ሰውነታቸው ተበልቶ እንደ ከብት ሲሸጥ ከዛም ተርፈው ወደነዚህ ሃገራት ቢገቡ የዚህ አይነት ችግር ሲደርስባቸው ይህ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለህዝብ ውርደትንና ሃዘንን ያሸከመ የወያኔ መንግስት ብልሹ አስተዳደር መሆኑን በመላው አለም የሚገኙ ኢትዮጵያን እንዲገነዘቡልን እንፈልጋለን።

ከዚህ በፊት ድህነት፣ ሙሰኝነት፣ ዘረኝነት፣ ጭቆናና ብዙ ብልሹ አሰራሮችን ስናወግዝ እና ስንታገል ብንቆይም ባሁኑ ሰዓት ግን በሳውድአረብያ በወገኖቻችን ላይ የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን ግፍ በማውገዝ የኢትዮጵያ ቱባ ባለ ስልጣናት ጉዳዩን ከቁብ ባይቆጥሩትም እኛ ግን አጽንኦት ሰተን የምንናገረው ይህ ግፍ እና ኢሰብአዊ ድርጊት ባስቸኩዋይ እንዲቆም በማለት ድርጅታዊ ተቃውሞዋችንን እናስተላልፋለን።


የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ

ጀርመን


ህዳር 13/2013


**Contact:** EPPFG - International <> Email: kirarayiso@googlemail.com <> www.eppfguard.com.